# ስስት ያደርሳል ከሞት

በኪዳነ ግርማይ

ቅንጅት በሥልጣን፣ ጅብ ደግሞ በሥጋ ሆድ አያስችላቸውምና ሁለቱም ስስትን ይጋራሉ። ቋንቋቸውም <<እንብላ ካላችሁ እንብላ፥ አንብላ ካላችሁም እንብላ፥ እንብላ፥ ...እንብላ>> ምንጊዜም እንብላ፥ እንብላ ብቻ ነው። ቅንጅቶች እርስ በራሳቸው፣ በስስት ውዳሴ-ከንቱ <<የቍርጥ ቀን ሰው፣ የቍርጥ ቀን ሰው>> እየተባባሉ ሲወዳደሱ ይሰማሉ። ምሥጢሩም ቁርጥ ወይም ቁርጠኝነት ማለት ሳይሆን የሚበላውን ቍርጥ ሥጋ ማለት እንደሆነ ከሚከተለው አጭር ድርሳን መረዳት ይቻላል። የስስት ድርሳኑም እንሆ።

ሰዎች ጅብን ጠርተው፣ ኢያ ጅብይ፣ የቍርጥ ሥጋ ይሰጥሃልና ተሎ ብለህ ይህችን መልእክት አድርስልን አሉት ይባላል። ጅቡ ደግሞ ሥጋ የሚለውን ቃል ስለሰማ፣ ተቻኵሎ ነገሩን ሳያጣራ፣ እሺ አላቸው። ሰዎቹ ቀጠሉ፡- ሥጋውን ግን ከጆሮህ ቈርጠን ነው የምንሰጥህ አሉት። ስስታሙም ጅብ ሥጋ እበላለሁ በሚለው ከንቱ ምኞት ልቡ ስለተዘጋ የገዛ ሥጋውን ከራሱ ጆሮ ቈርጠው እንደ ሚሰጡት አላወቀም። ምክንያቱም አልሰማቸውም፤ ልብም አላለም፥ አላስተዋለምም። ጅቡ መልእክቱን አድርሶ ከተመለሰ በኋላ፣ በውሉ መሠረት፣ ጆሮውን



ቆረጡትና ሰጡት። እሱም የገዛ ጆሮውን ሥጋ ብሎ በላው። ያ ጅብ፣ አተርፍ ባይ አጕዳይ እንዲሉ። ከዚያች ቀን ጀምሮ አካለ ጐደሎ ሆነ፤ ጤናም አላገኘም። ቆራጣ ስለሆነም ስሙ ቆሪጥ ተባለ። ባሄደበት ሁሉ ቆሪጥ፣ ቆሪጥ እያሉ ይጠሩታል።

ቅንጅት እና የቅንጅት ወገኖችም እንዲሁ እያንዳንዱ በተናጠል ቆሪጥ ከተባለው ጅብ፣



በፓርቲ ደረጃ ደግሞ ከጅብ መንጋ ተሽለው አልተገኙም። አዎ! ማመን በሚያስቸግር መልኩ ቅንጅቶች ከውጭ ወራሪ ኃይል፣ ከሻዕቢያው መንግሥትና ከተገንጣዮች የውስጥ ኃይላት ጋራ በመተባበር፣ ኢትዮጵያን በማተራመስና በማፈራረስ እኩይ ተግባር ላይ ተጠምደዋል። በምትኩም ቅንጅቶች በእነርሱ ቅዠት በፈራረሰችውና በተተራመሰችው ኢትዮጵያ ላይ በሻዕቢያ ተባርከው ለመንገሥ አሰፍስፈዋል።

የሻዕቢያ መንግሥትም ለጅብ መንጋው ቅንጅቶች የገዛ ጆሯችሁን ቆርጬ ሥጋ ብየ አበላችኋለሁ፤ ያች ጥንታዊት እና ታሪካዊት እያላችሁ የምትኵራሩባት ኢትዮጵያችሁም ዳግም እንደማታንሰራራ አድርጌ አፈራርሳታለሁ፤ በተለይ H.R 2003 በሚባለው Bill (ረቂቅ አዋጅ) ተጽዕኖ ምክንያት ልዑላዊነቷ የተደፈረና የተዋረደች አገር እንድትሆን አደርጋለሁ፤ ከሁሉም በላይ ሕዝቧ እንዲበታተን እጥራለሁ እያላቸው ነው። ቅንጅቶች ግን አሁንም ልብ አላሉም፣ አላስተዋሉምም።

ያ አረመኔው ክፉ ጕረቤት፣ ሻዕቢያ፣ ኢትዮጵያን ካተራመሰና መፈራረሷን ካረጋገጠ በኋላ፣ በሱ ፈቃድ የሚመራ፥ ጆሮው የተቆረጠ፥ እጁና እግሩ የሰለሉ፥ ደካማና የሻዕቢያ ቡችላ የሚሆን የቅንጅት መንግሥት ያቋቍማል ማለቱ ነው። ከቅንጅት ጆሮ ተቆርጦ ለራሱ ለቅንጅት የሚሰጠው ሥጋ ይህ ነው። ከሻዕቢያ የሚገኝ ቁም-ነገርና ውለታም ይህ ነው። ሻዕቢያ ይህንን እኩይ ተልእኮውን ሲፈጽም፣ ቅንጅቶች በውስጥም በውጭም መሪና ተባባሪ ሆነው ቢያገለግሉት፣ የክሕደት አክሊል ጭኖ እንደሚያነግሣቸው ቃል

ገብቶላቸዋል። ከጅብ ለማይሻሉ ሆዳም ቅንጅቶች ኢትዮጵያ ተቆርጣ ተቆራርጣ፥ ፈርሳና ተደራምሳ፥ ከተበታተነች በኋላ፣ በፍርስራሿ ላይ ይነግሡባት ዘንድ በሻዕቢያ ትሰጣቸዋለች ማለት ነው። ቅንጅቶችን ከጅብ ጋራ የሚያመሳስላቸው ተግባር ይህ ነው። እውነትም ይህ የጅብ ጠባይና የስስታሞች አስተሳሰብ መሆኑ ነው። ካልሆነ ቅንጅቶች በድርጅት ደረጃ ተደራጅተው *እትብታቸው የተቀበረባት፣ የገዛ አገራቸው፣ ኢትዮጵያን ለምን ሊከዷት ከጀሉ*? ይገርማል! ይህ አምላኬ እንደ ቅንጅት ከመራከስና በከሓዲነት ከመፈረጅ አድነኝ ያስብላል።

አዎ! የቁርጥ ቀን ልጆች ነን ባዮቹ ቅንጅቶች እኒሁ ናቸው። እነርሱ የያዙት ነገርም ሁሉ አደናጋሪ ነው። የአቋም መነሻና መድረሻ የላቸውም፤ እልኸኞች፣ የማያምኑና የማይታመኑ፣ ከሓድያን ናቸው። ለምሳሌ በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው፣ ወድያውኑ መሰባሰብ ሲጀምሩ፣ እርስ በራሳቸው በየመድረኩ፣ የቍርጥ ቀን ሰው፣ የቍርጥ ቀን ሰው ሲባባሉና ሲወዳደሱ ስንሰማ፣ አተረጓጐሙ ላይ አሳስተዉን ነበር። ምክንያቱም አባባላቸው *ቍርጥ* ነው ወይስ *ቁርጥ* ብለን ለመለየት አማርኛው ግልፅ አልነበረም። አሁን ግን የቅንጅት መንነትና ማንነት ግልጥልጡ ወጥቷል። ያለቍርጥ መኖር የማይችሉ፥ የሥልጣን ራብ ስሜታቸውን መግታት የተሳናቸው፥ የሃገር ክሕደት ወንጀል የፈጸሙ እና ለሆድ አደር የሆኑ *ሰው መሳይ ጅቦች* ናቸው። አዎ! ቍርጥ ሲያጡም እንሆ ሻዕቢያ በሳለው ቢላዋ እናት ሃገራችን፣ ኢትዮጵያን አርደው አወራርደው፥ ቈርጠው ቆራርጠው፥ ጠብሰውና አሳርረው ሊበሉዋት ያሰፈሰፉት *ከሐዲያን* ወይም *ጅቦች* ናቸው።

አዎ! <<*የጅብ ፍቅር እስኪቸግር*>> እንዲሉ፣ ጅብና ጅብ ስለማይተማመኑ ጐን ለጐን ይሄዳሉ እንጂ ፊትና ኋላ ሆነው አይሄዱም ይባላል። በስመ ቅንጅት በተሰባሰቡት ሰዎች መካከልም እንደዚሁ መተማመን የለም፣ ፍቅርም የለም፣ የዓላማ አንድነትም የለም። ስለሆነም በጐሪጥ እየተያዩ ጐን-ለጐን በመጓዝ ላይ ይገኛሉ። የቅንጅት አቋምና ዓላማም ስስት፣ ጥርጣሬ፣ መለያየት፣ እንደ ጅብ መበላላት፣ ቂም-በቀል፣ ክሕደት፣ ቅሌት እና ውርደት ብቻ ነው።

አዎ! <<*የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል*>> እንዲሉ፣ ገና ለገና በሰማይ ባለው ደመና፣ በእጅ ባልጨበጡት ሥልጣን ቅንጅት ከወዲሁ ሕዝቡን ማስፈራራት ጀመረ። በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝቦች <<*ከአሁኑ የጮኸ ጅብ አያሳድረንም*>>> ሲሉ ተቹበት። መተቸት ብቻም አይደለም አከ እንትትፍ ብለው ተፉት፥ ተፉበትም። ምክንያቱም ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ እንዲሉ፣ መንግሥታዊ በትረ ሥልጣን ቢጨብጡ በሕዝቡ ላይ የበቀል እርምጃ እንደሚወስዱ ከወዲሁ ዝተዋል፥ አውጀዋልም። ይህነን የሚያመለክት አንዱና ዋነኛው *የማይረሳው የታሪክ ጠባሳው* ደግሞ ያ *"ትግሬው ወደ መቀሌ፣ ንብረቱ ወደ ቀበሌ""* በማለት ሕዝቡን እንደሚበቀሉትና እንደ ጠላት እንደ ሚያሳድዱት በየአደባባዩ የተናገሩት ሓቅ ነው። በዚሁም አላቆሙም፡- በኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር፣ ሕዝቡ እርስበራሱ እንዲተላለቅ፣ እገሌ እገሌን በለው፥ ግደለው፥ እረደው በማለት ጠብ እንዲያነሳሳ አድርገዋል።

*ሶከ አመኬላው ቅንጅት፣ እንደ ሰይጣን፣ ሰላም አትባባሉ፥ በምንም አትደራረሱ፥ በኃዘንና በደስታ አትገናኙ፥ የእገሌን ጠበል አትቅመሱ በማለት የሕዝባችን ማኅበረ ሰባዊ ትስስርና ኢትዮጵያዊ ጨዋነቱን ለማምከን ጥሯል።*

የቅንጅቶች ዓላማም የብሔርና ብሔረ ሰብ ሕዝቦች መበቀል ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ

በሥርዓት አልበኝነት እንደ ሶማሊያ በአናርኪስት እየታመሰች እንድትኖር ነው። ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ በጐደና ነውጥና በዓመፅ ሕገ መንግሥቱንና መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከሥረ መሠረቱ ለመናድ ያደረጉት ሙከራ ራሱን የቻለ በቂ ምስክር ነው። ቅንጅት እንደ ፓርቲ ቢለካም ልኩን የማያውቅ፣ ክብሩንም የማይጠብቅ፣ ተስፋ የሌለው፣ ቊንጥንጥ እና ወራዳ ነው። አዎ! ጅብ የሚበላ ነገር ሲያገኝ ያለአቅሙ ይበላና በቊንጣን ይወጠራል፤ አቊነጥንጦም ያስታውከዋል፤ ያስታወከውንም ተመልሶ ይበላዋል ይባላል። የቅንጅቶች ክብርም እንዲሁ ነው። ቅንጅት ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ራእይና ሕዝባዊ እምነት የጐደለው፥ መነሻውና መድረሻው ሁሉ ቅጡ የጠፋበት፥ የነውራሞች ስብስብ ወይም የጅብ መንጋ እንጂ ፓርቲ ተብሎ ሊጠራ አይገባውም።

አዎ! በአማራጭ ፓርቲ ፍለጋ የምትቋምጡ፤
አልቅሱ፥ ዋይ ዋይ በሉ፥ እርማችሁን አውጡ፤
ቅንጅቶች ጅራቸውን እንዲቆረጡ፤
አጐንብሰው ለሻዕቢያ ሰጡ፤
ለዕለት ጉርስ ክብራቸውን ሸጡ፤
እዝነ ልቦናቸው በመቆረጡ፤
ይኸው ግራ ተጋቡ፥ ቅጥ አጡ።

አዎ! ቅንጅት እና ጅብ በሥጋ፤
በፓርቲ በብዱን የጅብ መንጋ፤
የሚተራመስ ለሥልጣን ፍለጋ፤
ዓላማ የሌለው ውዳቂው ፋንጋ ለፋንጋ፤
እንዲህ ነው ቅንጅት የሌለው ዋጋ።

ቅንጅቶች፣ ቅንጅት ወይ ቅንጅት፤
ኢትዮጵያዊ ሰው ነው? ወይስ የጅብ መዓት?
ዓላማው የጐደለው አንድነት፤
ሕዝባዊነቱ የራቀው እምነት፤
አንድነቱ የተለየው ውኅደት፤
ይህ ነው የጅብ መንጋው ቅንጅት?

በጅብ መንጋው ፓርቲ ቤት ***ቆሪጥ***፤
አሁን ምን አመጣው መደናገጥ፤
ቅንጅት፣ ቅንጅት፣ ሲይዙት መንቀጥቀጥ፤
ሲለቁት መፈርጠጥ፤
ጅሮው ሲቆርጡት **ፍጥጥ**።
ፍጥጥ፥ ፍጥጥጥ፥ ፍጥጥጥ፥ …ጥጥ።

<u>ስስት ያደርሳል ከሞት</u>

ስስታሙ ቆሪጥ የገዛ ጅሮውን በልቶ ሞተ።



ቅንጅትም ልክ እንደ ቆሪጥ ሙቷል። ቅንጅት መንፈስ ነው፤ ቅንጅት ፓርቲ ነው፤ ቅንጅት አይሞትም እያላችሁ የምትባንኑ ሰዎች ሁሉ ካንቀላፋችሁበት ተነሱና እርማችሁን አውጡ። አልሞተም አትበሉ፣ ቅንጅት ሞቷል። *ሞቱ ለኃጥእ ጸዋግ* እንዲሉ፣ የሞት ሞት፣ ክፉ ሞት ነው እንጂ መሞት ብቻም አይደለም። አዎ! ዋይ በሉ፥ እሪ በሉ፤ እንሆ ላልሰማችሁ መርዶ፦ ቅንጅት አብዶ፥ አብዶ፥ ባሕር ማዶ ሄዶ፥ ተዋርዶ፥ ክብሩን ሸጦ ነው የሞተው።

አዎ! በሀገር ክሕደት የመርገም ጨርቅ ተገንዞ፤
ክብሩን አጥቶ፥ የገዛ ጅሮውን በልቶ ተመርዞ፤
ሞት አይቀርም ቅንጅት ሞተ መጥፎ ስም ይዞ።

-----------------------ተፈጸመ-----------------------

እወ ተፈጸመ ናሁ የአስስት ድርሳን፤
እክሕደከ ቅንጅት መንፈሰ ጸብእ ወሰይጣን፤
---------- ለዓለመ ዓለም አሜን! ወአሜን። -------